# የአጠቃላይ ትምህርት

## የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር መመሪያ

(ረቂቅ)

መስከረም 2016
ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ

| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| መግቢያ | 1 |
| ክፍል አንድ | 2 |
| አጠቃላይ ሁኔታ | 2 |
| አንቀጽ 2፦ የቃላት ትርጓሜ | 2 |
| አንቀጽ 3፦ አስፈላጊነት | 3 |
| አንቀጽ 4፦ የተፈጻሚነት ወሰን | 4 |
| አንቀጽ 5፦ ዓላማ | 4 |
| አንቀጽ 6፦ መርሆዎች | 5 |
| ክፍል ሁለት | 7 |
| የተማሪዎች ምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር | 7 |
| አንቀጽ 7፦ የቅድመ አንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ | 7 |
| አንቀጽ 8፦ የአንደኛ ደረጃ ከ1-5 እና 6ኛ የክፍል ክፍል ዝውውር አፈፃፀም | 7 |
| አንቀጽ 10፦ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር | 10 |
| አንቀጽ 11፦ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች | 12 |
| አንቀጽ 12፦ የተፋጠነ የተማሪዎች የክፍል ክፍል ዝውውር | 13 |
| ክፍል ሶስት | 13 |
| ተከታታይ እና ማጠቃለያ ምዘና | 13 |
| አንቀጽ 13፦ ተከታታይ ምዘና | 13 |
| አንቀጽ 14፦ የመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት እና የአመቱ ማጠቃለያ ምዘና አፈፃፀም | 14 |
| ክፍል አራት | 15 |
| ክፍል ስለ ማቋረጥ፤ ስለ መድገም፤ ማስረጃ ስለ መስጠት እና ፈተና ስለማጭበርበር | 15 |
| አንቀጽ 15፦ ክፍል ስለ ማቋረጥ | 15 |
| አንቀጽ 16፦ ክፍል ስለ መድገም | 16 |
| አንቀጽ 17፦ በየክፍል ደረጃውና በየእርከኑ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች | 17 |
| አንቀጽ 18፦ ምዘና እና ፈተና ማጭበርበር | 17 |
| አንቀጽ 19፦ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት | 17 |
| ክፍል አምስት | 18 |
| የፈፃሚ እና ባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት | 18 |

**አንቀጽ** 20፦ *ፈፃሚ አካላት* ....... 18
**አንቀጽ** 21፦ *ባለድርሻ አካላት* ....... 20
**ክፍል ስድስት** ....... 21
**ልዩ ልዩ ጉዳዮች** ....... 21
**አንቀጽ** 22፦ *ተፈጻሚነት ማይኖራቸው አሠራሮችና ልማዶች* ....... 21
**አንቀጽ** 23፦ *መመሪያውን ስለ ማሻሻል* ....... 21
**አንቀጽ** 25፦ *መመሪያው ተግባራዊ የሚሆነበት ጊዜ* ....... 21

## መግቢያ

መንግስት ባለፉት ሶስት አስርት አመታት ለአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት በትምህርት ተደራሽነትና ፍታዊነት መሻሻል ታይቷል። ሆኖም ግን የትምህርትን ጥራት ከማረጋገጥ አኳያ አሁንም ሰፊ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። ለትምህርት ጥራት መጓደል አንደኛው ምክንያት ምዘና፣ ፈተና እና የክፍል ዝውውር በተገቢው መንገድ ባለመከናወኑ ነው።

በአጠቃላይ ትምህርት የሚከናወነው የምዘና ስርዓት በዋነኛነት የተመሰረተው በተከተታይ ምዘና እና በማጠቃለያ ፈተና ነው። በመሆኑም  የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት እና ሥነምግባር ለመለካትና ለመገምገም የሚያስችል የፈተናና የምዘና ሥርአት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ለመተግበር በልዩ ልዩ መንገዶች ስራ ላይ የሚውሉ የተከታታይና የማጠቃለያ ምዘናዎችን መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡፡

በሁሉም ክልሎች እና በከተማ አስተዳደር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር የሚከናወነው ወጥነት በሌለው መንገድ ነበር፡፡ እንዲሁም እየተተገበረ ያለው ግምገማና ምዘና በየትምህርት እርከኑ በሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎትና አስተሳሰብ ለማስጨበጥና ለእድገት እና ብልጽግና ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትን አንኳር የትምርት አይነቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ በሀገራችን ያለው የምዘናና ዝውውር ስርአት የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ ካለው ጠቀሜታ አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ላይ የማይገኝ ሲሆን ተማሪዎችንም በአለም ሀገራት ካሉ አቻዎቻቸው ጋር ለመወዳደር ከማስቻል አኳያም ትልቅ ክፍተት አለበት፡፡

በመሆኑም በአጠቃላይ ትምህርት በየክፍል ደረጃው እና በየትምህርት እርከኑ በሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ተማሪዎች የጨበጡትን እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ያጎለበቱትን አመለካከት ወጥ በሆነ መንገድ በመመዘን ተማሪዎችን ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውር ለማከናወን እንዲቻል ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

መመሪያው ስድስት ክፍሎች ሲኖሩት በክፍል አንድ አጠቃላይ ሁኔታዎች፣ በክፍል ሁለት የተማሪዎች  ምዘና እና  ከክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር፣ በክፍል ሶስት ተከታታይ እና ማጠቃለያ ምዘና፣ በክፍል አራት ክፍል ስለ ማቋረጥ፤ ስለ መድገም፤ ማስረጃ ስለመስጠት እና ፈተና ስለማጭበርበር፣ በክፍል አምስት የፈፃሚ እና ባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት እንዲሁም በክፍል ስድስት ልዩ ልዩ ጉዳዮች  ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አንድ
# አጠቃላይ ሁኔታ

**አንቀጽ 1፡- አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በአጠቃላይ ትምህርት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና ከክፍል ክፍል የዝውውር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2፡- የቃላት ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **ተከታታይ ምዘና** ማለት ከማጠቃለያ ፈተና በፊት ባሉት የወሰነ-ትምህርቱ የትምህርት ጊዜያት በተለያዩ ዘዴዎች በየጊዜው በተከታታይ የሚካሄድ የምዘና አይነት ነው።
2. **የማጠቃለያ ፈተና** ማለት በወሰነ-ትምህርቱ ማጠናቀቂያ ላይ በጽሁፍ ወይንም በተግባር የሚሰጥ የመጨረሻ ፈተና ነው።
3. **ሀገር አቀፍ ፈተና** ማለት በትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ነው።
4. **የመማር ብቃት** ማለት ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብና በተግባር የሚከታተሉትን ትምህርትና ስልጠና ሲያጠናቅቁ የሚላበሱት፣ የሚያሳዩት እና የሚተገብሩት የዕውቀት፣ የክህሎትና የባህሪ መገለጫ ነው።
5. **የክፍል ክፍል ዝውውር** ማለት በአንድ የትምህርት ዘመን ተማሪዎችን በተከታታይ ምዘና እና በማጠቃለያ ፈተናዎች ውጤት መሠረት ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ የሚደረግ የዝውውር ሂደት ነው፡፡
6. **የትምህርት እርከን** ማለት በአጠቃላይ ትምህርት ስላሉት አራት እርከኖች የሚገልጽ ሲሆን እነዚህም ቅድመ አንደኛ ደረጃ (ደረጃ 1 እና ደረጃ 2)፣ አንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍሎች)፣ መካከለኛ ደረጃ (7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች) እና ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍሎች) ናቸው፡፡
7. **አንኳር የትምህርት ዓይነት** ማለት ለአንደኛ እና ለመካከለኛ ደረጃ የትምህርት እርከኖች ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ እና የሒሳብ ትምህርት ዓይነቶች ናቸው፡፡ ለሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ እና የሒሳብ ትምህርት ዓይነቶች ናቸው፡፡

8. **የተፋጠነ የክፍል ክፍል ዝውውር** ማለት አንድ ተማሪ ለመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት የታቀደውን ትምህርት በማጠናቀቅ በተከታታይ ምዘና እና በማጠቃለያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገቡ ወደ ቀጣዩ ክፍል በሁለተኛው ወሰነ-ትምህርት እንዲዛወር የሚደረግበት አሰራር ነው።
9. **የቀለም ትምህርት** ማለት በቅድመ አንደኛ ደረጃ በተቀናጀ ሥርዓተ ትምህርት የሚሰጠውን ትምህርት ጨምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ባሉት የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች የሚሰጡ የቋንቋ፣ ሂሳብ፣ ተፈጥሮ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ፣ ሥነጥበባት፣ የግብረገብና የዜግነት፣ የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ፣ የመረጃና የተግባቦት ቴክኖሎጂ ትምህርት ዓይነቶች ነው፡፡
10. **የትኩረት መስክ፡-** ማለት በ11ኛ እና 12ኛ ክፍሎች ከቀለም ትምህርቶች ጋር የሚሰጡ የማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ መረጃ ቴክኖሎጂና ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ግብርና፣ ጤና ሳይንስ፣ ቢዝነስ ሳይንስ፣ ቋንቋና ማህበራዊ ሳይንስ እና ሥነጥበባት ከሥራና ሙያ መስክ ጋራ የተያያዙ የሙያ ትምህርቶች ዘርፍ ነው፡፡
11. **የሥራና ተግባር ትምህርት** ማለት ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ በ7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍሎቸ በተለያዩ የትኩረት መስኮች ስር የሚሰጥ ተማሪውን በቅጥርና በግል ሥራ እንዲሰማራ የሚያበቃው ትምህርት ነው፡፡
12. **የትምህርት ዘመን** ማለት በሁለት ወሰነ-ትምህርት የተከፈ ሆኖ ከመስከረም 2 እስከ ሰኔ 30 ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡
13. **ፈተና አስተዳደር** ማለት ፈተና ደንብና ስርዓትን ተከትሎ እንዲሁም ደህንነቱና ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ ተማሪዎች እንዲፈተኑት በክልል/በከተማ አስተዳዳር ትምህርት ቢሮ ወይም በትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት የሚከናወንበት የአሰራር ሥርዓት ነው፡፡

## አንቀጽ 3፡- አስፈላጊነት

*ይህን መመሪያ ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያት፡-*

1) የመንግስትን ስርዓተ ትምህርት አሟልተው የመተግበር ግዴታ ባለባቸው በሁሉም ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ 12ኛ ክፍል በመደበኛው፣ በማታ እና በርቀት መርሃ ግብሮች ትምህርት በሚሰጡ ተቋማት ወጥ የሆነ የምዘና አዘገጃጀት እና የክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤

2) እንደ ሀገር ጥራቱና ተገቢነቱ የተረጋገጠ የተማሪዎች ምዘና ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
3) የምዘና አተገባበርን ማሻሻል የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ ከሚከናወኑ ቁልፍ ተግባራት አንዱ በመሆኑ፤
4) ወጥ የሆነ የፈተናና ምዘና ሥርአት ባለመኖሩ ተማሪዎች ከቦታ ወደ ቦታ በሚደረግ ዝውውር የሚያጋጥማቸውን ችግር መቅረፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤
5) መምህራን እንዲሁም የትምህርት ባለሙያዎችና አመራሮች ጥራቱን የጠበቀ ምዘና ለመተግበርና ለማስተግበር የሚያደርጉትን ጥረት በህግ መደገፍ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

**አንቀጽ 4፡- የተፈጻሚነት ወሰን**

1) ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚደረገው ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ 12ኛ ክፍል በመደበኛ እንዲሁም በማታው እና በርቀት መርሃ ግብሮች ትምህርት በሚሰጡ ተቋማት ነው፤

2) መመሪያው ከዓለም አቀፍና ከውጭ ማህበረሰብ ትምህርት ቤቶች በስተቀር በመንግስትና በሌሎች በሁሉም አይነት ትምህርት ቤቶች/ተቋማት/ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5፡- ዓላማ**

**1) አጠቃላይ ዓላማ**

በሀገር አቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ ትምህርት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ 12ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በወሰነ-ትምህርቱ ወይም በአመቱ ማጠቃለያ ፈተና በየደረጃው ባሉ የትምህርት ተቋማት በሚሰጡ ፈተናዎች ያገኟቸውን እውቀት፣ ክህሎት እና አዎንታዊ አመለካከት በመመዘን ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል እና የትምህርት እርከን የሚሸጋገሩበት ወጥነት ያለው የአሰራር ስርአት መዘርጋት ነው፡፡

**2) ዝርዝር ዓላማ**

ሀ) በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች እየተተገበረ ያለውን ወጥነት የሌለው የክፍል ክፍል ሽግግር የሚተካ የአሰራር ስርአት ለመዘርጋት፣

ለ) ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎችን በየደረጃው በሚሰጡ ምዘናዎች ብቃታቸውን ለመመዘን የሚያስችል ሀገር ዓቀፍ የክፍል ክፍል ሽግግር የውጤት መቁረጫ ለመወሰን፣

ሐ) አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ እና በየደረጃው በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች፣ በሀገር ዓቀፍ እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በሚሰጡ የመማር ብቃት ምዘናዎች ተወዳዳሪ የሆኑ ተማሪዎችን ለማፍራት፣

መ) ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ያቋረጡትን ትምህርት ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል እንዲሁም ከአንድ ት/ቤት ወደ ሌላ ት/ቤት ተዛውረው ትምህርታቸውን መቀጠል የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር፣

ሠ) ተማሪዎች በየደረጃው ለሚያጠናቅቋቸው ክፍሎች ወይም የትምህርት ደረጃዎች ህጋዊ የትምህርት ውጤት ማስረጃ የማግኘት መብታቸውን ለማረጋገጥ፣

ረ) የመምህራን የትምህርት አቀራረብ እና ስርአተ ትምህርቱ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ግብአቶችን ለማግኘት፣

ሰ) በሀገር አቀፍ ደረጃ በየትምህርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ በየደረጃው ያለውን መጠነ መድገም እና መጠነ ሽግግር መረጃ ለቀጣይ መሻሻል እና የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ግብአት ለማሰባሰብ፣

ሸ) ተማሪዎች በቀጣይነት በውሳኔያቸው መሰረት መርጠው መከታተል ለሚፈልጓቸው የትምህርት መስኮች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር፣

ቀ) በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በምዘና እና ውጤት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ግድፈቶችን ለማስተካከል የሚያስችል ስርአት ለመዘርጋት፣

## አንቀጽ 6፡- መርሆዎች

የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ሽግግር ስርአት የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል ይኖርበታል፡፡

ሀ) **ጥራት፡-** በየደረጃው የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት በማጠናከር የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የትምህርት ቤቶች የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ስርአት እንደ አንድ ወሳኝ ግብዓት ወስደው ስራ ላይ ያውላሉ፡፡

ለ) **ፍትሀዊነት፡-** የተማሪዎች ምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ያለምንም ልዩነት በተማሪዎች ውጤት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ልዩ ፍላጎት ላላቸው እና ለሴት ተማሪዎች ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ሐ) **ለላቀ ውጤት አልሞ መስራት፡-** የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ሥርዓት ትግበራ የየደረጃውን ተማሪዎች ውጤት እና ባህርይ በማሻሻል የነገን ሀገር ተረካቢ ዜጎችን የሚያፈራ ይሆናል።

መ) **አሳታፊነት፡-** የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ሂደት እና አፈጻጸም የትምህርት ባለሙያዎችን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ይሆናል፡፡

ሠ) **ቀጣይነት ያለው መሻሻል፡-** የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለትምህርት ባለሙያዎች በተማሪው ቀጣይ የትምህርት ሁኔታ እና መሻሻል ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ይሆናል፡፡

ረ) **ተአማኒነት፡-** የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ሂደት እና ውጤት አሰጣጥ ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ እና ያለምንም አይነት አድልዎ እና ወገናዊነት ለሁሉም ተማሪዎች በስራቸው እና ባመጡት ውጤት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

ሰ) **ተወዳዳሪነት፡-** የምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር ሥርዓት ትግበራ በአንድ ትምህርት ቤት ወይም በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ትምህርታቸውን በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ከሚከታተሉ ተማሪዎች ጋር የሚኖርን ውድድር የሚያበረታታ ይሆናል፡፡

ሸ) **ግልጽነት፡-** በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተሰጣቸውን ሀላፊነት እና ተግባር መሰረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወን እና ያከናወኑትን ተግባር የሚመለከታቸው አካላት በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተማሪዎች ምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር

### አንቀጽ 7፡- የቅድመ አንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

ሀ) ከቅድመ አንደኛ ደረጃ አንድ ወደ ደረጃ ሁለት እና ወደ አንደኛ ክፍል የሚደረገው ዝውውር የህጻናትን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ በስርዓተ ትምህርቱ የተቀመጡ የተከታታይ ምዘናዎችን ተግባራዊ በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፡፡

ለ) በዚህ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች የአመቱን ትምህርት ማጠናቀቃቸውን በተከታታይ ምዘና በማረጋገጥ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ደረጃ ይዛወራሉ፡፡

### አንቀጽ 8፡- የአንደኛ ደረጃ ከ1-5 እና 6ኛ የክፍል ክፍል ዝውውር አፈፃፀም

#### 1) ከ1ኛ - 3ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

ሀ) ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ባሉት ክፍሎች ከክፍል ክፍል የሚደረገው ዝውውር በተከታታይ ምዘና እና የማጠቃለያ ፈተና ውጤት ላይ በመመሥረት ይሆናል፣

ለ) በተከታታይ ምዘና ከሚያዘው 70% እና በትምህርት ዘመኑ ግማሽ ዓመት እና ማጠቃለያ ላይ ከ30% በሚሰጠው ፈተና በአማካይ በሁሉም ትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ሲያመጡ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራሉ፣

ሐ) ከ1ኛ-3ኛ ክፍሎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል ለመዘዋወር የሚያስችላቸውን ውጤት ካላገኙ ትምህርት ቤቱ የቀጣዩ ትምህርት ዘመን መጀመሪያ ወር ላይ ተማሪዎች ባላሟሉት ትምህርት ዓይነት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ በድጋሚ በሚሰጥ ፈተና የሚጠበቅባቸውን ውጤት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ እንዲዛወሩ ይደረጋል፣

መ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ቁጥር (ሐ) በተጠቀሰው መሰረት አስፈላጊው ክትትል እና ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ቀጣዩ ክፍል መዛወር ያልቻሉ ተማሪዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ በነበሩበት ክፍል እንዲደግሙ ይደረጋል፣

## 2) የ4ኛ እና የ5ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

ሀ) የተማሪዎች የክፍል ዝውውር በሁሉም የትምህርት አይነቶች 60% በተከታታይ ምዘና እና 40% በትምህርት ዘመኑ ግማሽ ዓመት እና ማጠቃለያ ላይ በሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና በአጠቃላይ ከ 100% የሚያገኙትን ውጤት በማስላት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ለ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ1 አንኳር ባልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 51% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

መ) በ2 አንኳር ባልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሠ) በ3 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ/ች ተማሪ 54% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ረ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

## 3) የ6ኛ ክፍል ክልላዊ የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

ሀ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ለ) በ1 አንኳር ባልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 51% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ2 አንኳር ባልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

መ) በ3 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ 54% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሠ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

## አንቀጽ 9፦ የመሀከለኛ ደረጃ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

### 1) ከ7ኛ ክፍል ወደ 8ኛ ክፍል ዝውውር፦

ሀ) የተማሪዎች የክፍል ዝውውር በሁሉም የትምህርት አይነቶች 40% በተከታታይ ምዘና እና 60% በትምህርት ዘመኑ ግማሽ ዓመት እና ማጠቃለያ ላይ በሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና በአጠቃላይ ከ100% የሚያገኙትን ውጤት በማስላት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ለ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ወደ 8ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ1 አንኳር ያልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 51% ካገኘ ወደ 8ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

መ) በ2 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ 8ኛ ይዛወራል፡፡

ሠ) በ3 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 54% ካገኘ ወደ 8ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

ረ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

### 2) የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ

ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል የሚደረገው ሽግግር በሚመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

ሀ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ወደ 9ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

ለ) በ1 አንኳር ያልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ 9ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ2 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 53% ካገኘ ወደ 9ኛ ይዛወራል፡፡

መ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

### 3. የሁለተኛ ደረጃ ከ9-10፣ 11ኛ እና 12ኛ የክፍል ክፍል ዝውውር

### አንቀጽ 10፦ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር አተገባበር

1) **የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ**

ሀ) የተማሪዎች የክፍል ዝውውር በሁሉም የትምህርት አይነቶች 40% በተከታታይ ምዘና እና 60% በትምህርት ዘመኑ ግማሽ ዓመት እና ማጠቃለያ ላይ በሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና በአጠቃላይ ከ100% የሚያገኙትን ውጤት በማስላት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ለ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ1 አንኳር ያልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 51% ካገኘ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይዛወራል፡፡

መ) በ2 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ ቀጣቀዩ ይዛወራል፡፡

ሠ) በ3 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 55% ካገኘ ወደ ቀጣቀዩ ይዛወራል፡፡

ረ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

2) **የ11ኛ ክፍል የተማሪዎች ምዘና እና የክፍል ክፍል ዝውውር ሁኔታ**

ሀ) የተማሪዎች የክፍል ዝውውር በሁሉም የትምህርት አይነቶች 30% በተከታታይ ምዘና እና 70% በትምህርት ዘመኑ ግማሽ ዓመት እና ማጠቃለያ ላይ በሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና በአጠቃላይ ከ 100% የሚያገኙትን ውጤት በማስላት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ለ) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ያገኘ ወደ 12ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

ሐ) በ1 አንኳር ያልሆነ የትምህርት ዓይነት ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 52% ካገኘ ወደ 12ኛ ክፍል ይዛወራል፡፡

መ) በ2 አንኳር ያልሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ውጤት ያመጣ ተማሪ አማካይ ውጤት 54% ካገኘ ወደ 12ኛ ይዛወራል፡፡

ሠ) በአንኳር የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ያላመጣ ተማሪ ወደ ቀጣዩ ክፍል አይዛወርም፡፡

ረ) ተማሪዎች በመረጡት አንድ የሥራና የተግባር ትምህርት መስክ አጥጋቢ እውቀት እና ክህሎት መጨበጣቸውን ለማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይኖራል። ለክፍል ደረጃው በየሥራና የተግባር ትምህርት መስክ ተማሪዎች በክፍልና በመስክ ደረጃ የተማሯቸው የትምህርት አይነቶች ይሆናሉ።

ሰ) ከ11ኛ ክፍል ወደ 12ኛ ክፍል ለመዘዋወር የሚያስችላቸውን ውጤት ያላመጡ ተማሪዎች በክረምት ወቅት በግል ተዘጋጅተው በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት የድጋሜ ፈተና ወስደው በዝውውር መመሪያው መሰረት የተቀመጠውን መስፈርት ካሟሉ ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡

3) **የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በተመለከተ፦**

አስራ አራት አመት የሚወስደውን አጠቃላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች የአጠቃላይ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት ፈተና ይወስዳሉ። ይህ የ12ኛ ክፍል መጨረሻ ፈተና ዋነኛ አላማ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው ሥርአተ ትምህርቱ ተመሳሳይ በመሆኑና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ ተማሪዎች የቀሰሙትን የዕውቀትና የክህሎት ደረጃ ለማወቅ፣ በሰለጠኑበት የስራና ተግባር ትምህርት በቂ ክህሎት መጨበጣቸውን እና ለስራ ዓለም ያላቸውን ዝግጁነት በብቃት ማረጋገጫ ለመመዘን እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ያላቸውን የዝግጅት ለመመዘን እና ፈተናውን በበቂ ሁኔታ ያለፉትን ከፍተኛ ትምህርት እንዲከታተሉ ለማድረግ ነው።

በመሆኑም የ12ኛ ክፍል ተማሪ በሚሰጠው አገር አቀፍ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና ወስዶ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገባው፦

ሀ) ትምህርት ሚኒስቴር ሚያስቀምጠውን ዝቅተኛ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ነጥብ ያሟላ፤

ለ) በአንኳር የትምህርት ዓይነቶች ከ50% በታች ያላገኙ።

ሐ) ዓይነ ስውር ተማሪዎች ከሒሳብ በስተቀር እንደማንኛውም ተማሪ ዝቅተኛ ማለፊያ ነጥብ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መ) ተማሪዎች በአንድ የሥራና የተግባር ትምህርት መስክ ጥናት ማጠናቀቃቸውንና በዚያም መስክ መመረቃቸውን ለማረጋገጥ የሚካሄድ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይኖራል። ለዚህም ሲባል የሚወሰዱት የትምህርት አይነቶች በመስክ ደረጃ ተማሪዎች የተማሯቸው ይሆናሉ። ይህንን ፈተና ማለፍና መመረቅ በቀጥታ በከፊል በሰለጠነ ወይንም በሰለጠነ ሰራተኛ ደረጃ ወደ ስራ ዓለም ለመሰማራት ወይንም ከትኩረት መስክ ጋር ከተያያዙ የትምህርት አይነቶች በተጨማሪ እንግሊዝኛንና ሂሳብን ጨምሮ በመውሰድ አግባብነት ባላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብቶ ለመማርና ለመሰልጠን ያስችላል።

## አንቀጽ 11፦ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ፍላጎታቸውን መሠረት በማድረግ በተመረጡ የትምህርት አይነቶች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ በማድረግ እና ተስማሚ የምዘና ስልቶችን በመጠቀም ከክፍል ክፍል ይዘዋወራሉ ፡፡

1) ልዩ ፍላጎት ያለው ተማሪ በተለያዩ ግላዊ እና ህጋዊ ምክንያቶች ትምህርቱን ከመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና በፊት ቢያቋርጥ የትምህርት ማስረጃ አይሰጠውም፡፡ በቀጣዩ አመት ትምህርት ቤቱ ወይም ሌላ ማንኛውም የመንግስት ት/ቤት ተማሪውን ተቀብሎ የማስተማር ሀላፊነት አለበት፡፡

2) ልዩ ፍላጎት ያለው ተማሪ በዝቅተኛ ደረጃ የተቀመጠውን የማለፊያ ውጤት ካላስመዘገበ በክረምት ወራት በመምህራን እና የት/ቤቱ አመራር ድጋፍ ተደርጎለት በድጋሚ ተመዝኖ የማለፊያ ውጤቱን ማሟላቱ ሲረጋገጥ ወደ ቀጣዩ ክፍል ይሸጋገራል፡፡

**አንቀጽ 12፦ የተፋጠነ የተማሪዎች የክፍል ክፍል ዝውውር**

1) አንድ ተማሪ በመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት ውጤቱ በአማካይ 95% እና በሁሉም የትምህርት አይነቶች 90% እና በላይ ውጤት ካስመዘገበ ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲዛወር ይደረጋል፡፡

2) ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተገለጸው ተፈጻሚ የሚሆነው በ 3ኛ፣ 4ኛ እና 9ኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪዎችን በመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት ትምህርት ባስመዘገቡት ውጤት ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲዘዋወሩ ለማድረግ በቅድሚያ የተማሪዎቸ ወላጆች/አሳዳጊዎቸ ስምምነት ሲኖር ነው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ተከታታይ እና ማጠቃለያ ምዘና

**አንቀጽ 13፦ ተከታታይ ምዘና**

ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማር ሂደት ዋና አካልና ተማሪዎችን በሂደት የመመዘኛ ስልት ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝና የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ የትምህርት አቀባበልና አካሄድ በመመዘን ተማሪዎችን ለማገዝ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ቤቱ ላይ ጠቃሚ ውሳኔ ለመስጠት መረጃ የሚሰብሰብበት የምዘና ስርዓት ነው፡፡

ስለዚህ በተከታታይ ምዘና የተለያዩ የምዘና መሳሪያዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ለመለካት፣ ለማሳደግ፣ ተማሪዎችን ለመመዘን፣ ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት ሲከናወን የሚከተሉትን ጉዳዮች ማስታወስና መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሀ) የተማሪዎችን የመማር ውጤታማነት ለመለካት የሚያመቹ የተከታታይ ምዘናዎችን በአይነት በቁጥር እና በጊዜ አቅዶ መተግበር ያስፈልጋል፤

ለ) ተከታታይ ምዘናዎች ሲዘጋጁና ሲተገበሩ ለየትምህርት ዓይነቱ የተቀመጠውን ጥቅልና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የመማር ብቃት መስፈርቶች እንዲሁም የየይዘቶቹን ባህሪና የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል፤

ሐ) በዚህ መመሪያ በአንድ የትምህርት ወሰነ-ትምህርት ለተከታታይ ምዘና የተቀመጠው ድርሻ ሙሉ በሙሉ መሸፈኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤

መ) የተከታታይ ምዘና ውጤቶች በአግባቡ ሊመዘገቡ፣ ሊጠናቀሩ እና በአስረጂነት ሊጠበቁ ይገባል፤

ሠ) የተከታታይ ምዘና ውጤት እና ግብረመልስ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለተማሪዎች መሰጠት ይኖርበታል፤

ረ) ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች የሚሰጡ የማጠቃለያ ፈተናዎች በዝርዝር መግለጫ ሰንጠረዥ /table of specification/ መሰረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤

**አንቀጽ 14፦ የመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት እና የአመቱ ማጠቃለያ ምዘና አፈፃፀም**

የማጠቃለያ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ሁኔታና ውጤታማነት በመረዳት ጠቃሚ ውሳኔዎችን ለመስጠት ስራ ላይ ከሚውሉ የምዘና አይነቶች አንዱና ዋንኛው ነው፡፡ በማጠቃለያ ምዘና የተማሪዎች የመማር ውጤታማነትን ለመፈተሽ፣ ለመለካትና ቁልፍ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ሲታሰብ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማስታወስና መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሀ) ይህ ምዘና የትምህርት ወሰነ-ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ለ) የማጠቃለያ ምዘና በጽሁፍ በሚሰጥ ፈተና አማካኝነት የሚካሄድ ሲሆን እንደየ ክፍል ደረጃው ቢያንስ ምርጫ፣ እውነት ሀሰት፣ ማዛመድ፣ ክፍት ቦታ መሙላት እና ገለጻ ከመሳሰሉት የጥያቄ አይነቶች መካከል ከ2 እስከ 4 መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሐ) የጥያቄው መጠን ለ4ኛ እና 5ኛ ክፍል ከ25-30፣ ለ7ኛ ክፍል ከ30-40፣ ከ9ኛ እስከ 11ኛ ላሉ ክፍሎች ከ50-60፣የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና በየትምህርት አይነቱ በሀገር ደረጃ ከሚዘጋጀው ዋና ፈተና ጋር እኩል ቁጥር ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

መ) በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በተከታታይ ምዘና የተገኘ ውጤትን ወይም በማጠቃለያ ፈተና የተገኘ ውጤትን ወደ 100% በመቀየር ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲሸጋገሩ ማድረግ አይቻልም፡፡

ሠ) አንድ ተማሪ በአንድ ወሰነ-ትምህርት ለክፍል ደረጃው ከተመደበው የትምህርት ጊዜ ከ12 ቀናት እና በላይ የትምህርት ቀናት ካልተከታተለ ለመንፈቀ ዓመቱ ማጠቃለያ ፈተና መቀመጥ አይችልም፤

ረ) ተማሪዎች ዝግጅት ማድረግ እንዲያስችላቸው ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ፈተናውን አስመልክቶ አጠቃላይ መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፤

## ክፍል አራት

## ክፍል ስለ ማቋረጥ፤ ስለ መድገም፤ ማስረጃ ስለ መስጠት እና ፈተና ስለማጭበርበር

### አንቀጽ 15፦ ክፍል ስለ ማቋረጥ

1) አንድ ተማሪ በትምህርት ዘመኑ ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶ በተለያዩ ግላዊ እና ህጋዊ ምክንያቶች ትምህርቱን ከመጀመሪያው ወሰነ-ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና በፊት ቢያቋርጥ የትምህርት ማስረጃ አይሰጠውም፡፡ ትምህርት ቤቱ በቀጣዩ አመት ተማሪውን ተቀብሎ የማስተማር ሀላፊነት አለበት፡፡

2) አንድ ተማሪ በትምህርት ዘመኑ ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶ የመጀመሪያውን ወሰነ-ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ወስዶ በተለያዩ ከአቅም በላይ ግላዊ እና ህጋዊ ምክንያቶች ትምህርቱን ቢያቋርጥ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ወሰነ-ትምህርት የትምህርት ውጤት ማስረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3) ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ትምህርት ቤቱ ወይም ማንኛውም የመንግስት ት/ቤት ተማሪውን በሁለተኛው ወሰነ-ትምህርት ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

4) አንድ ተማሪ በአንድ ወሰነ-ትምህርት ለ12 ቀናት ከትምህርት ገበታው ከቀረ ትምህርቱን እዲቀጥል አይፈቀድለትም፡፡

5) አንድ ተማሪ በወሊድ ምክንያት 15 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ካረፈች በኋላ ትምህርቷን መቀጠል ትችላለች፡፡ ሆኖም ግን 16 ቀናትና ከዚያ በላይ ከትምህርት ገበታዋ ከቀረች ከዘመኑ ትምህርት ትታገዳለች፡፡

6) በዚሁ አንቀጽ በተራ ቁጥር (5) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣዩ ዓመት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ትምህርቷን መቀጠል ትችላለች፡፡

**አንቀጽ 16፦ ክፍል ስለ መድገም**

1) አንድ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ክፍል ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ወይም በአንድ ክፍል ከሁለት ጊዜ በላይ ከደገመ ከትምህርት ቤቱ ይሰናበታል፤

2) አንድ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ከሁለት ጊዜ በላይ ከደገመ ከትምህርት ቤቱ ይሰናበታል፤

3) በ6ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች ላይ በሚሰጡ ፈተናዎች የማለፊያ ነጥብ ካላገኘ ለአንድ ጊዜ በትምህርት ቤቱ በመደበኛነት ትምህርቱን እንዲከታተል ይደረጋል፤

4) አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ከ12ኛ ክፍል ውጪ በአንድ ክፍል ከሁለት ጊዜ በላይ ከደገመ እና በተከታታይ ክፍሎች ከደገመ ከትምህርት ቤቱ ይሰናበታል፡፡ ትምህርት ቤቱም ይህን የሚገልፅ ማስረጃ ለተማሪው/ዋ መስጠት ይኖርበታል፡፡

5) ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ተማሪው በሌላ የመንግስት ትምህርት ቤት በመደበኛ ተማሪነት ገብቶ መማር አይችልም። ሆኖም ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ትምህርቱን መቀጠል ይችላል፡፡ በየደረጃው ያለው የትምህርት መዋቅር ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 17፦ በየክፍል ደረጃውና በየእርከኑ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች

1) በስምንተኛ እና 12ኛ ክፍል መጨረሻ የሚሰጠው የትምህርት ውጤት ህጋዊ መግለጫ /ትራንስክሪፕት /ሀገር ዓቀፍ/ክልላዊ ፈተና የሚሰጥበት ደረጃም ከሆነ የክልላዊ ፈተና ውጤት ህጋዊ መግለጫ ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መብቃታቸውን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

2) በስምንተኛ ክፍል መጨረሻ የሚሰጠው የትምህርት ማስረጃ በክልላዊ የሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 18፦ ምዘና እና ፈተና ማጭበርበር

1) አንድ ተማሪ በመማር ማስተማር ሂደት ለሚፈጽማቸው ግድፈቶች እና ማጭበርበር ማለትም በቡድን ስራ፣ በአጫጭር ፈተናዎች፣ በማጠቃለያ ፈተና የሌላ ተማሪ ስራን በመገልበጥ ወይም በመኮረጅ ወይም ሆን ብሎ ሌሎች ተማሪዎች ከእሱ እንዲኮርጁ በማመቻቸት፣ ተግባር ላይ የተሰማራ በፈተና ወቅት የተከለከሉ ነገሮችን ይዞ የገባ መሆኑ በመምህራን እና በትምህርት ቤቱ አመራር ሲረጋገጥ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ 19፦ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

1) ተማሪዎች በውጤት ሪፖርት ካርድ በተመዘገቡ ውጤቶች ላይ ቅሬታ ካላቸው ካርዱን የተቀበሉበትን ቀን ሳይጨምር ባሉት ሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ቅሬታቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በተመሳሳይ ከውጤት አመዘጋገብ ጋር በተያያዘ ወላጆች/አሳዳጊዎች ትምህርት ቤቱ የውጤት ሪፖርት ካርድ ለተማሪዎች ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ቅሬታቸውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3) ትምህርት ቤቱም ከተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ከማጠቃለያ ውጤት አሞላል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በአንድ ሳምንት ግዜ አጣርቶ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት

## የፈፃሚ እና ባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

**አንቀጽ 20፦ ፈፃሚ አካላት**

**1) ትምህርት ሚኒስቴር**

ሀ) የተማሪዎች የምዘና አተገባበርና ከክፍል ክፍል ሽግግርን አስመልክቶ ሀገር አቀፍ መመሪያዎች ያዘጋጃል፤

ለ) የተማሪዎች ምዘና እና ከክፍል ክፍል ዝውውር በሀገራዊ መመሪያው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፣

ሐ) በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ርምጃዎችን ይወስዳል፤ ከምዘና አተገባበርና ከተማሪዎች ዝውውር ጋር የተገናኙ ጥናቶች ያደርጋል፤

መ) ዋና ዋና ባለድርሻዎችን ያሳተፈሀገራዊ የምዘና እና ከክፍል ክፍል ሽግግር መመሪያ ለመከለስና ለማዳበር የሚያስችሉ ምክክሮችን ያደርጋል፤

ሠ) ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት የሚቀርብለትን የእርማት ውጤት መነሻ በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ነጥቦችን ይወስናል፤

**2) የክልል /ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች**

ሀ) ሀገር አቀፉን የምዘናና ዝውውር መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የምዘናና ዝውውር መመሪያ ትግበራውን ይከታተላል፤

ሐ) የ6ኛ ክፍል ማጠናቀቅያ ፈተና አዘገጃጀት እና የምዘና አተገባበር መመሪያ ያዘጋጃል፤

መ) የ6ኛ ክፍል መልቀቅያ ፈተና አዘገጃጀትና አስተዳደርን አስመልክቶ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ አጠቃላይ አተገባበሩን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ) የ8ኛ ክፍል ፈተናን ያዘጋጃል፤ ያስተዳድራል የውጤት ማስረጃ ይሰጣል፤

ረ) የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና አተገባበር ሒደትን ይከታተላል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን ያደርጋል፤

ሰ) የዝውውር መመሪያ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

3) **የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት**

ሀ) ለ8ኛ ክፍል ፈተና የፈተና አወጣጥ ስታንደርድ አዘጋጅቶ ለክልሎች ይልካል፤

ለ) በአገር አቀፍ ደረጃ 12ኛ ክፍል ወጥ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፤

ሐ) ምዘናዎችን ከክልል እና የከተማ አስተዳደሮች ት/ቢሮዎች ጋር በመሆን ያስተዳድራል፤

መ) የብሔራዊ ፈተናዎችን ያርማል፣ ውጤት ያጠናቅራል፣ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

ሠ) ከብሔራዊ ፈተናዎች ውጤት አሰጣጥ ጋር ለተያያዙ ቅሬታዎች ምላሽ ይሰጣል፤

4) **የዞን/የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት**

ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የምዘናና የዝውውር መመሪያን ተግባራዊ ደርጋል፤

ለ) በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የዝውውር መመሪያ ላይ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

ሐ) የዝውውር መመሪያውን አተገባበር ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤

መ) የዝውውር መመሪያ አተገባበር ላይጥናት በማድረግ በግኝቶቹ መሰረት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤

5) **ትምህርት ቤቶች**

ሀ) አገር አቀፍ የዝውውር መመሪያን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) በምዘና አተገባበር እናየተማሪዎች ዝውውር መመሪያ ላይ ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል፤

ሐ) በአተገባበር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየትለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

መ) በመመሪያው መሰረት የትምህርት ማስረጃና የውጤት መግለጫ /Report Card/ ለተማሪዎች ይሰጣል፤

ሠ) ከተማሪዎች ምዘናና ውጤት ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፤

**አንቀጽ 21፦ ባለድርሻ አካላት**

**1) መምህራን**

ሀ) በአገር አቀፉ መመሪያ መሰረት ተማሪዎችን ይመዝናል፤ ውጤት ያጠናቅራል፤ ተማሪዎችን ውጤት ለት/ቤቱ ያቀርባል፤

ለ) ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን ከተማሪዎች ምዘናና ውጤት ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን በመቀበል ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሐ) የፈተና ምስጢራዊነትን ይጠብቃል፤

መ) የተማሪዎችን የመማር ሁኔታና የምዘና ውጤት ሚስጥራዊነት ይጠብቃል፤

ሠ) የተማሪዎችን የምዘና ውጤት በማደራጀትና በመተንተን የውጤት መግለጫ /Report Card/ ያዘጋጃል፤ ለተማሪዎች ይሰጣል፤

**2) ወላጆች/አሳዳጊዎች**

ሀ) የምዘናና የተማሪዎች ዝውውር መመሪያን መረዳት ይጠበቅባቸዋል፤

ለ) ከልጆቻቸው የመማር ውጤታማነት ጋር በተገናኘ ከመምህራንና ከትምህርት ቤት ሀላፊዎች ጋር በቅርብ መነጋገርና በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፤

ሐ) ልጆቻቸው በመመሪያው መሰረት መመዘናቸውን እና የተጠቃለለ የውጤት መግለጫ መቀበላቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

መ) ከምዘና፣ ከውጤት እንዲሁም ከዝውውር ጋር የተገናኘ ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታቸውን በቃል በማስረዳትና በጽሁፍ በማቅረብ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው፤

### 3. ተማሪዎች

ሀ) በምዘና እና በክፍል ክፍል ዝውውር መመሪያ ላይ ግንዛቤ የማግኘት መብት አላቸው፤

ለ) ለየትኛውም አይነት ምዘና ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤

ሐ) ከምዘና እና ከዝውውር ጋር የተገናኘ ማንኛውም ችግር ሲገጥማቸው ለመምህሮቻቸው ወይንም ለትምህርት ቤቱ አመራር ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፤

መ) በአመቱ የትምህርት ማጠናቀቅያ ላይ የተጠቃለለ የውጤት መግለጫ የማግኘት መብት አላቸው፤

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### አንቀጽ 22፦ ተፈጻሚነት ማይኖራቸው አሠራሮችና ልማዶች

1) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያዎች እና የተለመዱ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

2) የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት በተለያዩ ጊዚያት እና የክፍል ደረጃዎች የሚያካሂዳቸው ምዘናዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ሳይቀላቀሉ ተግባራዊ መሆን ይገባቸዋል፤

### አንቀጽ 23፦ መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ትምህርት ሚኒስቴር እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

## አንቀጽ 25፦ መመሪያው ተገባራዊ የሚሆነበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ        ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።